# ጎንደር ዩኒቨርስቲ

# ተማሪዎች መተዳደሪያ

# የዲስፕሊን መመሪያ

## ሰኔ /2000 ዓ/ም

Student Dean's Office
University of Gondar

D-2

10.1.5. የዩኒቨርስቲዉ ተማሪ ያልሆነን ግለሰብ በመኝታ ክፍል ዉስጥ ማስተኛት/ማስተናገድ (ለመኝታ ክፍሉ አባላት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሠጣል)

10.1.6 ምግብና መኝታ ከዉጪ ለመጠቀም ገንዘብ ወስደዉ ከዩኒቨርስቲዉ አገልግሎቱን ሲጠቀሙ መገኘት

10.1.7.በዩኒቨርስርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ አደንዛዥ ዕጽና (ሄሮይን፣ኮኬይን፣ማሪዋና ሺሾ ወዘተ እና አልኮልነት ያላቸዉን መጠጦች ይዞ መገኘት /መጠቀም/፡፡

10.1.8. ያለፈቃድ በተቃራኒ ፆታ መኝታ ህንፃዎች መግባትና ማስገባት ወይም ሁኔታዎችን አመቻችቶ ተቃራኒ ጾታን ወደ መኝታ ሕንጻ ማስገባት ወይም ለማስገባት መሞከር፡፡( በሁለቱም እርምጃ ይወሰዳል)

10.1.9. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ቅድመ ዕዉቅና ያላገኘ ስብሰባ ማካሄድ

10.1.10 አድማ ማሣደም ወይም ለማሠደም መሞከር ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ በሌላም ቦታ ብጥብጥና ግጭትን የሚያስከትል ፅሁፎችን መለጠፍ

10.1.11. የተቃራኒ ፆታ ተማሪዎችን በንግግር፣ በፅሁፍ፣ በሃይል ወዘተ ማስፈራራት ማስቸገር፣

10.1.12. ሰክሮ በመኝታ ክፍልና በአካበባዉ ወይም በመማሪያ ክፍልና በላብይረሪ ሲረብሽ መገኘት

10.1.13. በጋራ መገልገያ መኝታ ክፍል፣ኮሪደር፣ ወይም መመገቢያ አዳራሽ በህብረት የፀሎት ስነ-ስርዓት ማድረግ

10.1.14. ማጭበርበር ( በትምህርት እና በአገልግሎት አሠጣጥ ላይ )

10.1.15. በዩኒቨርስቲዉ አግባብ ባለዉ አካል ተፅፎ የተለጠፈ ማስታወቂያ መቅደድ፣ መሠረዝ፣መደለዝና መገንጠል

10.1.16. ያልተፈቀዱ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን (ከብሪይ፣ሻማ፣ስቶቭ፣ቦይለር ሌሎች ተቀጣጣይ ነገሮችን (ቤንዚን) በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ መያዝና መጠቀም

10.1.17. የዩኒቨርስቲዉ ንብረት ከሆነዉ መፅሕፍት ዉስጥ የቀደደ፣ የሰረዘ፣የደለዘ፣የገነጠል እንዲሁም በላቦራቶሪና በወርክሾፕ መሣሪያዎችን ከጥቅም ዉጭ ያደረገ፣ በምግብ ቤና በመኝታ ቤት የሚገለገልባቸዉን ቁሳቁሶች ሆን ብሎ የሰበረ ያጠፋ ንብረቱን መልሶ ይተካል/እርምጃም ይወሰድበታል፡፡



የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት
Student Dean's Office
University

10.1.21. ሌሎች መሰል የዲስፕሊን ግድፈቶችን መፈፀም

## 10.2. እስ፡፡ ሁለት የት/ት ዓመታት ከት/ት ገበታ የሚያሳግዱ የዲስፕሊን ግድፈቶች

10.2.1. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ማንኛዉንም ዓይነትስርቆት ሲፈፅም እጅ ከፈንጅ የታያዘ፡፡

10.2.2. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

10.2.3. በሰካርም ሆነ በሌላ መልኩ ተደፋፍሮ ተቃራኒዉ ፆታ ህንፃ ዉስጥ ሲረብሽ የተገኘ/ች

10.2.4. በተግባር ት/ት በሙያዉ ተጠቅሞ በግለሰቦች (በበሽተኞች፣ አስታማሚዎች ወዘተ) ላይ ከሙያ ስነ-ምግባር ዉጪ የሆነ ተግባር መፈፀም፣

10.2.5. ማንኛዉም አይነት ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሣሪያ (ጩቤ፣ ቢላ የጦር መሣሪያ፣ ወዘተ ይዞ መገኘት

10.2.6 ፊርማን በመኮረጅ ወይም ሰንዱን በመደለዝ ፣ በመሰረዝ ለማጭበርበር መሞከር ወይም የተጭበረበረ ማስረጃ ማቅረብ፣

10.2.7 በልዩ ልዩ ምክንያቶች ክሊራንስ ጨርሰዉ ከትምህርት ገበታቸዉ የታገዱ ተማሪዎችን የመኝታና የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ

10.2.8 በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ እና ዉጭ የሚሰጡ ፈተናዎችን በመፈተኛ አዳራሽ ዉስጥ ተገኝቶ ለሌላ ተማሪ ሲፈተን መገኘት እንዲሁም እንዲፈተንለት ያደረገ ተማሪ፡፡

10.2.9 በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ከተፈቀደዉ ያለባበስ ስርዓት ዉጭ የፖለቲካ፣ የዘርና የሃይማኖት ግጭቶችን ሊያስነሱ የሚችሉ ልብሶችን ለብሶ መገኘት

10.2.10 ተገቢዉን ክፍያ ሳይፈጽም ወይም የወጭ መጋራት ሳይፈርም መማር ወይም የአገልግሎት ተጠቃሚ ሆኖ መገኘት (የተገኘ)

10.2.11. የዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ በዛቻ ማስፈራራትና የድብደባ ሙከራ ማድረግ

10.2.12 ከዩኒቨርስቲዉ ተማሪዎችና ሠራተኞች ጋር ጥል ፈጥሮ መደባደብ

የተማሪዎች ... Student Dean's Office University of ...

12.7. ክስ የሚመሰረቱባቸው ጉዳዮች

የዲስፕሊን ክስ ተመስርቶ በዲስፕሊን ኮሚቴ የሚመረመረው ተማሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 የተመለከቱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የዲስፕሊን ጉድለት ፈጽሟል ተብሎ ክስ ሲመሰረትበት ነዉ፡፡

## አንቀጽ 13 . <u>የክስ አመሰራረትና ስርጭት</u>

13.1. የክስ ምስራታ

13.1.1 ክስ እንዲመሰረትና ጉዳዩ በዲስፕሊን ኮሚቴ እንዲጣራ የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት ዋና ክፍል ኃላፊ፣ የጥበቃና ደህንነት ክፍል ኃላፊ፣ የተማሪዎች ህብረት ወይም አግባብ ያላዉ ኃላፊ ወይም አካል ሊመሰረት ይችላል፡፡

13.1.2 አስፈላጊ መረጃዎችንም ማጠናከር

13.1.3 ተማሪዎች አገልግሎት ሃላፊ ወይም የጥበቃ ደህንነት ክፍል ሃላፊ፣ የምግብ ቤት ሃላፊ፣ የተማሪዎች ህብረት/መማክርት እርግጥ ጥፋት ተፈጽሞአል ብሎ ካመነ በጽሁፍ ለረዳት ተ/ዲ ሪፖርት ማድረግ አለበት በጽሁፍ ሪፖርት በሚደረግበትም ወቅት ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ እንዲቀርብ ሃሳብ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡ ሪፖርቱም ስለ ክሱ ሁኔታ ማብራሪያ ከተማሪው ጋር የተደረጉት ውይይቶች እና አሰፈላጊው መረጃም ማካተት ይኖርበታል፡፡

13.1.4 ረዳት የተማሪዎች ዲንም ሪፖርቱ እንደደርሰው ከዚህ በፊት ተማሪው ጥፋት አጥፍቶ የነበረ መሆኑን እና አለመሆኑን ይመረምራል፡፡ሪፖርቱንም ከመረመረ በኃላ የሚወስደው ርምጃ እንዳለ ወይም በማሻሻል በሰባት ቀን ዉስጥ የሚፈለጉትን መረጃዎች በማጠናከር ተማሪዉ ተመዝግቦ ወደሚማርበት ፋካሊቲ/ኮሌጅ/ኢንስቲትዩት/ ዲን ጽ/ቤት ወይም የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት በጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

13.1.5. ፋካሊቲ/ኮሌጅ/ኢንስቲትዩት ዲን የደረሰዉን ክስና መረጃ በመመልከት የተፈፀመዉ የዲስፕሊን ግድፈቱ ከትምህርት ገበታ ሊያሳግደዉ የሚችል ወይም የትምህርት መረጃ የሚያሲዝ ወይም ከትምህርት ገበታ የሚያስባርር ከሆነ በዲስፕሊን ኪሚቴ እንዲታይ ይመራል ፡፡ ረዳት ዲኑም ጉዳዩ ለተማሪዎች ዲን በግልባጭ ያሳዉቃል፡፡



የተማሪዎች Student Dean's Office University of

13.2. ክስ ስርጭት

13.2.1. የኮሚቴው ሰብሳቢ ማስረጃዎች ተጠናቀው ሲቀርቡ ተከሳሹ ለቀረበበት ጥፋት መከላከያ ለማቅረብ እንዲችል፣

13.2.1.1. ተከሳሹ የቀረበበትን ዝርዝር ጥፋት፣

13.2.1.2. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚቀርብበትን ቀንና ሰዓት በመግለጽ የክስ ጽሁፍ በደረሰኝ ወይም በማስታወቂያ ለተከሳሹ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

13.2.1.4. ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስና የመከላከያ ማስረጃ የሚያቀርብበት ጊዜ የክሱ ጽሁፍ ከደረሰው ቀን ወይም በማታወቂያ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ በ5 ቀን ማቅረብ አለበት፡፡

13.2.1.5. ተከሳሹ በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ እያለ በዲስፕሊን ኮሚቴ ቀጠሮ ላይ ካልተገኘ ድጋሚ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚገኝበት ቀንና ሰዓት ተገልጾ የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያ ይወጣል፡፡ ማስታወቂያውም ለሦስት ቀን በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ እንዲቆይ መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ተከሳሹ ካልቀረበ ግን በሌለበት ለክሱ የቀረበውን ማስረጃ የዲስፕሊን ኮሚቴው መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለፋካልቲ/ኮሌጅ/ኢንስትቲዩት/ ዲን ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 14. ክስ የሚቋረጥበት ሁኔታ

14.1. በግል አቤቱታ ክስ ብቻ የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ግድፈቶች ዉሳኔዉ በዲስፕሊን ኮሚቴ ከመሰጠቱ በፊት ሊቋረጡ ይችላሉ፡፡ ክስ እንዲቋረጥ የሚቀርብ ጥያቄ በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ግድፈት ዓይነቶች በወንጀል ህግ አንቀጽ 212 በተደነገገዉ መሠረት በተመሣሣይ ሁኔታ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

14.2. በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የዲስፕሊን ግድፈቶች ክሶች በማናቸዉም ሁኔታ ሊቋረጡ አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 15 - የችሎቱ አካሄድ

15.1 የዲስፕሊን ኮሚቴ ሰብሳቢ ሂደቱን እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ሰብሳቢዉም ሥነስርዓትና ህጉን የማስጠበቅ ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡



Student Dean's Office

## አንቀጽ - 22 - ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ ደንብ ከሰኔ 19 /2000 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይህ ደንብ 1/3 ኛው የዩኒቨርስቲዉ ሰኔት እንዲሻሻል የቀረበዉን ጥያቄ ሲደግፍ ደንቡ በሴኔት ታይቶ ሊሻሻል ይችላል፡፡

Student Dean's Office